# <u>የዘንዶ ሱባዔ?</u>

*(Corrected Version)*



ምስል:- በርዝመትና በስፋት ከሱ እኩል የሆነውን ዘንዶ ሲውጥ


ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

nigatuasteraye@gmail.com


ነሐሴ ፳፻፪ ዓ.ም.

***<u>ማሳሰቢያ:-</u>*** *የዚህን አመት የፍልሰታን ሱባዔ በመጨረስ ላይ ነን። ይሁን እንጅ በዘንድሮዋ ሱባዔ በቨርጅንያ የተከሰተው ነገር የዘንዶን ሰባዊዔ የሚያንጸባርቅ ነው። ስለዚህ ይህች ጦማር የዚህን አመት ሱባዔ ለማስታወስ ተዘጋጅታ የቀረበች ናት።*

# መግቢያ

ሱባዔ:- በሰው፤ በቦታና በሰአት ስለሚከናወን የሶስቱም ማለትም የሰአት፤ የሰባዊነትና የመካን ድምር ነው። ሱባዔ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጥልቅ፤ ረቂቅና ምጡቅ ግንዛቤ አለው። በመንፈሳችንና በሥጋችን መካከል ያለውን ሚዛን አለመሰበሩንና አለማጋደሉን፤ በፈጣሪያችንና በራሳችን መካከል፤ በህዝባችንና በራሳችን መካከል ያለንን ግንኙነት የምንፈትሽበት ነው። በሩቅና በቅርብ ያለውን አካባቢያችንን ማየት የምንችልበት ተራራ ነው። ውስጣዊ ህሊናችንን የምናይበት ረቂቅ መስታወት ነው። የራቀውን አቅርቦ የረቀቀውን አጉልቶ የሚያሳየን፤ እመቀ እመቃት፡ አየረ አየራት፡ ያሉትን ሁሉ ፍጥረታት የምንፈትሽበት ተራዛሚ መነጽር ነው።

ሱባዔ:- በሰው ብቻ የተወሰነ አይደለም። በደማቸው ሞቃትነትና ቀዝቃዛነት የሚለያዩ ፍጥረታት በየደረጃቸው ሱባዔ ይገባሉ። የፍጥረታትን ቅደም ተከተል በመጠበቅ የደመ ሞቃት እንስሳትንና፤ የዘንዶን ሱባዔ ከዳሰሰን በኋላ፤ የዘመናችን በተለይም የመነኮሳት ሱባኤ ከጥንታዊት ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሱባዔ ተቀይሮ፤ ከደመ ሞቃት እንስሳት ምን ያህል እንደራቀና ወደ ዘንዶ ሱባዔ እንደተቀረ በማነጻጸር፤ ይህ የዘንዶ አይነት ሡባዔ የማይታረም ባለበት የሚቀጥል ከሆነ፤ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ሁሉ ወንዱም ሴቱም በተለይ ትዳር ያፈረሰ በዝሙት በሌብነት በዘራፊነት የተከሰሰ ሁሉ ቆቡን እያጠለቀ፤ ምንኩስና ቁምስና ወደ ተላበሰ ቅስናና ሊቀ ጳጳስና እኛም እንግባ ብሎ መነሳቱ መፍትሄው ይመስለኛል። ሁሉንም አይተን ከምዳሜ ለመድረስ ከደመ ሞቃት እንስሳት ሱባዔ እጀምራለሁ።

# የእንስሳት ሱባዔ

በዚህች ጦማር የምናተኩረው በዘንዶ ሱባዔ ላይ ቢሆንም፤ የሚያድጉ የሚያረጁ የሚሞቱ ደመ ሞቃት እንስሳትም ሰባኤ አላቸው። ሥጋቸው እንዲበሉ የተፈቀዱት እንስሳት ቀኑን ሲሰበስቡ የዋሉትን ከሆዳቸው ወደ አፋቸው መልሰው በማምጣት በማመንዥክ ሱባዔ ይገባሉ። እኛ ሰዎች የምናመነዥከው አእምሯችን የቋጠረውን ሀሳብ ነው። ከሳረ በላዎች እንስሳት እንለያለን። የዋጠውን እያራገፈ እንደገና ለመዋጥ ከሚቅነዘነዝ ዘንዶም እንለያለን። ጥልቀቱንና ይዘቱን በዚህ ጥናት ለተሰማሩ ጠበብቶች ልተወውና፤ ሰባዊ ሱባዔን በጉሉህ መረዳት እንችል ዘንድ፤ የዘንዶን ሱባዔ በቅድሚያ ለመግለጽ እሞክራለሁ።

# የዘንዶ ሱባዔ

ሱባኤ፤ ሰው ጉሉሁንና ረቂቁን የሚታየውንና የማይታየውን ፈተና (challenge) አሸንፎ የሚወጣበት ስልት ስለሆነ ተጠልፎ ከወደቀበት ከዘንዶ ተለይቶ አይታሰብም። ስለዚህ ከሰባዊ ሱባኤ በፊት ሰው ተፈትኖ የወደቀበትን ዘንዶን መመልከቱ ሰባዊ ሱባኤን ስንመለከት በጥልቅ እንድንረዳው ያግዘናል።

ዘንዶ ደመ ቀዝቃዛ ነው። ሰውነቱን እንደ ወቅቱ ይለዋወጣል። ስለ ሰውነቱ ሙቀት፤ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት እንደ ዘመናውያን ሊቃውንት "በ50 ዲግሪ ፋራናይት ያወርደዋል" አይበሉ እንጅ፤ ከፍና ዝቅ እንደሚያደርገው ይናገራሉ። የዋጠው ከሰውነቱ ጋራ እስኪወሀድና፤ የተሸከመው አሮጌ ሰውነቱ ሲከብደው ለማስወገድ ራሱን ይደብታል። (ሱባዔ ይገባል)። የድበታውን ጊዜ (ሱባዔውን) ጨርሶ አሮጌ ገላውን ሸልቅቆ ካስወገደና ስባቱንም ካቃጠለ በኋላ፤ ባካካባቢው አየር ንብረት እየተገፋ ባዲስ ኃይልና ጉልበት የሚውጠውን ፍለጋ በመቅበዝበዝ ይንቀሳቀሳል። ዘንዶ ያለመደውን አያውቅም። ይልቁንም ያለመደውን ይውጣል። የሚያመነጨው የሙቀት ሃይል እንደሌሎች እንስሳት ከሚመገበው አይደለም። ባካባቢው አየር ንብረት ላይ የተመሰረተ ነው።

ስለ ዘንዶ ባህርይ እጅግ በጣም ያስገረመኝ፤ የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አባቶች "ዘመን ሲከፋ ሰው እርሱ በርሱ የሚባላ ዘንዶ ይሆናል" ብለው ሲናገሩ የሰማሁትን፤ የተፈጥሮ ሳይንስ ሊቃውንት "በርዝመትና በስፋት ከሱ እኩል የሆነውን ዘንዶ ሌላው ዘንዶ ይውጠዋል" ብለው የገለጹትን በተግባር ማየቴ ነው። ማረጋገጥ ከፈለጉ፤ *[ይህን* እባብ እባን ሲውጥ የሚያሳይ ቪዲዮ ]: *በመጫን ይመልከቱ*:: ቀጥለን ሰባዊ ሱባኤን በጥሞና እንመልከት።

# ሰባዊ ሱባኤ

ክርስቶስ "ሰው በዳቦ ብቻ አይኖርም" (ማቴ ፬:፬) ብሎ ስለ ሰባዊነት ባህርይ ተናግሯል። ይህ ንግግር ከመለኮታዊ እና ከሰባዊ ውህደት የመነጨ ስለሆነ መለኮት የማያጥፈው ሰው የማይሽረውና የማያሻሽለው በግድ መሆን ያለበት ኩነት ነው። ስለዚህ ሰው ገደሉን ሳያይ፤ ሳሩን ብቻ እያየ ከደል የሚገባ እንስሳ ሆኖ፤ ወይም የሚውጠውን በመፈለግ ተቅበዝባዥ ዘንዶ ሆኖ የተፈጠረ አይደለም።

ቅዱስ ጳውሎስ "መብልዕ ለከርሥ። ወከርሥኒ ለመብልዕ። ወእግዚአብኄር ይስዕሮሙ ለክሌሆሙ" (፩ ቆሮ ፮:፲፫) ማለትም:- "ምግብ ለሆድ ነው። ሆድም ለምግብ ነው። እግዚአብሔር ግን ሁለቱንም ያጠፋቸዋል"። ይህም ማለት፤ በሆዳምነት ሱስ ከሰባዊነት ባህርይ ወደ ደመ ቀዝቃዛው ዘንዶነት መቀየር ነው። አርአያነታችን የዘንዶ ሳይሆን የመለኮት ነውና፤ እግዚአብሔር ለራሱ አርአያ ቀናኢ በመሆኑ ይቆጣል። ይቀጣል።

በዚህ ብኩን ዓለም ውስጥ ኑሮን ለማሸነፍ መባክንና መቃተታችን ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው የክርስቶስን ነገረ መስቀል (ሱባዔ) ያስረሳናል። (ገላት ፫፡፩)። ስለዚህ ሊቃውንት አበው "ንትመየጥ፤ ንትባደር፤ ናፍጥን ለንስሐ"( ሃ አ ም ፴፯፡፪. ፲፩. ፲፬) ማለትም፡- ከሆዳምነት ወደ ሱባዔ እንመለስ፤ ለንስሀ አንዘግይ፤ እናፍጥን፤ በሱባዔ ለሚገኝ በረከትና ጸጋ እንወዳደር በማለት አጠንክረው ተናገሩ።

ክርስቶስ "ሸክማችሁ የከበደባችሁ ወደኔ ኑ" ብሎ ከራሱ በቀር ማንም ሊከፍትልን የማይችለውን የሱባዔ በር ከፍቶልናል። ከዚህም በመነሳት ሐዋርያት "መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለም"(የሐዋ ፬፡፲፪) እያሉ አስተምረዋል። ሐዋርያትን የተከተሉ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እነ ባስልዮስም "ዝንቱ ውእቱ ንጉሠ መላእክት ወሊቃነ መላእክት ወይእኅዝ ኃይላተ ወያነጽህ ኩሎ ወይመልክ ኩሎ ፍጥረተ"(ም ዕ ፴፫፡፵፯) " የሊቃነ መለእክት ንጉሥ ሃይልን የሚቆጣጠር ሁሉን የሚያነጻ ፍትረቱን የሚገዛ ክርስቶስ ነው። አድኖናል አጽድቶናል። አጽድቆናል። " እያሉ አስተማሩ። ቅዱስ ጎርጎርዮስም "ኢኮነነ ክርስቶስ እኅወ በግብር ሐዲስ አላ ለቢሶ ሥጋ ዚአነ በተዋህዶ ዘኢይትነገር" ማለትም፡- በማይመረመር መለኮታዊ ጥበቡ ያዳነን ከሰባዊነታችን በራቀ በሩቅና ረቂቅ መንገድ ሳይሆን የሚዳሰሰውን ሰባዊነታችን ከመለኮቱ ጋራ በማዋህድ ነው" እያለ ተናገረ። (ሃ አ ፴፰፡፫)። ይዚህ ሁሉ ትምህርት መነሻ የተከናወነው በሱባዔ ቀመር ነው። (ገላ ፬፡፬)።

ምንም እንኳ ክርስቲያኖች፤ በጥምቀት ከክርስቶስ ጋራ ሞተን እንደተቀብረን፤ ከአሮጌው ሰውነትም በመላቀቀ አዲስ ሰውነት እንደለበስን ብናምንም፤ በዚህ ዓለም ስንኖር በተቀደሰው ጋብቻ የተመሰረተው ትዳር የሚያስከትለውን ሀላፊነት ለመወጣት በምናደርገው መባከንና መቃተት፤ ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንደተናገረው በሱባዔ የተከናወነልንን የክርስቶስን ነገረ መስቀል ያስረሳናል። ይሸፍንብናል። (ገላት ፫፡፩)።

አውቀንም ሆነ ሳናውቅ ሰው ልንጎዳ እንችላለን። እንሳሳታለን። አንሳሳትም ማለት ደግሞ በዚህ ዓለም አንኖርም ማለት ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን። እውነትም በኛ የለም" እንዳለውም፤ የበለጠ መሳሳት ነው። ሱባኤ ኑዛዜ ነውና፤ ሱባዔ ገብተን "በኃጢአት ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ" አምላክ ከተሳሳትንበት እንድንመለስ የሚረዳን በሱባኤ ነው። "ኃጢአት አላደረግንም ብንል፤ ሐሰተኛ እናደርገዋለን። ቃሉም በኛ ውስጥ የለም (፩ኛ ዮሐ ፩፡፰—፲)" ስለዚህ ሱባኤ አያስፈልገንም ማለት ስህተት ነው።

ይህን የተገነዘበ ዮሐንስ አፈወርቅም "ሶበ ንኤብስ ለእግዚ ኩሎ ዕለተ ንትነሣእ እንከ እንዘ ለንስሀ እንዘ ሕያዋን ንሕነ በውስተዝ ዓለም(ሃ ፰፩፡፲፯) ብሏል። ማለትም፡- በእለታዊ ተግባራችን ስንባክን አውቀንም ሳናውቅም በምድር ሰውን፤ በሰማይ አምላክን እንበድላለን እናሳዝናለን። ስለዚህ በህወት እስካለን ድረስ የንስሀ (የሱባዔ) ጊዜ ሊኖረን ይገባል። ክርስቶስ ከፍሎልኛል በማለት ሱባዔ አያስፈልገኝም ማለት፤ ከወደቅንበት ተነስተን እንድንገባ ክርስቶስ በምሥጢረ ተዋህዶ የከፈተልንን በር መካድ ነው። በየእለቱ ለምንፈጽማቸው በደሎች ክርስቶስን ተባባሪና ተካፋይ ማድረግና ወደ ዘንዶነት ተንሸራት መግባትን ያስከትላል።

በእምነት ውስጥ ሳለን ለሚገጥመን ውድቀት ቅዱስ ጎርጎርዮስ "ወአንስአነ በጽድቀ ትንሣኤሁ እምነ ሙታን ወአርኀወ ለነ ኆኃተ ንስሐ" (ሃይ ፴፮፡፴፰) እንዳለው የምንወስደው ድርሻ አለነ። ማለትም፡- በትንሳዔው ቅድስና ከተቀደስን በኋላ ብንወድቅ እራሳችንን እንድንመረምር የንስሀ በር ከፈተልን። ይህም የተከፈተልን በር፤ ሳር ከሚበሉ እንስሳትና ከዘንዶ የምንለይበትን የሰባዊነታችንን ሚዛን ለመፈተሸ የምንገባው ሱባኤ ነው። ራሳችንን ከምንፈትሽባቸው ሱባዔዎቻችን አንዷ የፍልሰታ ሱባዔ ናት።

# ፍልሰታ

ስለ ፍልሰታ ሱባዔ ሳስብ ሊቃውንት አባቶች የሚናገሯቸው ብዙ ትዝታዎች ይመጡብኛል። በመግቢያ ላይ "ሱባዔ፡- በሰው፤ በቦታና በሰአት ስለሚከናወን የሶስቱም ማለትም የሰአት፤ የሰባዊነትና የመካን ድምር ነው" እንዳልኩት ፍልሰታ በኛና በፈጣሪ፤ እንዲሁም በኛና በቀሩት ፍጥረታት መካከል ያለውን ልዩነት የምናስብበትና የምናሰላስልበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅትም የጋስጫው አባ ጊዮርጊስ ፈጣሪንና ተፈጥሮን ያደነቁበትን ድርሰት ለምናስበውና ለምናሰላስለው መመሪያያችን አርገን እንጠቀምበታለን። ድርሰቱም የሱባዔን ሁለንተና የምንዳስስበትን ሰአት ጊዜና ወቅት ስላካተተ ሰአታት ይባላል። ፍልሰታን *አስመልክቶ የተጻፈውን ማንበብ ከፈለጉ ለማንበብ ቀጥሎ ያለውን ሰንሰለት ይጫኑ።* ፍልሰታ]

በፍልሰታ ሱባዔ በአንገታችን ነጠላ እየቋጠሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከላኩን እናቶች ጋራ የምናስታውሳቸው ብዙ ቅዱሳን አባቶች አሉን። አባቶች ስልም፤ ቆሞስ አባ እያሉ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የእባብ መንጋ የሚለቁባትን አባ ፋኑዔልን የመሳሰሉትን ማለቴ አይደለም። በንጽህና በቅድስናና በመልካም ምሳሌ ሆነው፤ ሳር ከሚያመሳኩት እንስሳት፤ እርስ በርስ ለመባላት ከሚያሳምጥ ሆዳምነት (ዘንዶነት) እርቀው፤ ለቅድስና ለዘላቂ ነገር ለህዝብ ለሃይማኖት ባደረጉት ተጋድሎ ትዝታና ቅርስ አውርሰውን ያለፉትን እንደነ አባ ጊዮርጊስ የመሳሰሉትን ማለቴ ነው (፩ኛ ቆሮ ፬፡ ፲፫) ክርስቶስ "ሰው በዳቦ ብቻ አይኖርም" ብሎ የሰውን ኑሮ ከሳረ በላዎች እንስሳትና ከዘንዶ ለይቶ የተናገረውን የተረዱ አባቶች ማለቴ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች "የሚሻለውን ነገር እፈተነ "ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝ የጽድቅ ፍሬ ሞልቶባችሁ ለክርስቶስ ቀን ተዘጋጅታችሁ ቅኖችና አለ ነውር እንድትሆኑ የሚሻለውን ነገር ፈትናችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ እጸልያለሁ "( ፊል ፩፡፲፩)። እንዳለው፡- በፍልሰታ ሱባዔ፤ ከታች አምናው ሱባዔ፤ ባምናው ሱባኤ፤ካምናው ሱባኤ ደግሞ በዘንድሮው ሱባዔ ምን እንዳሻሻሉ ራሳቸውን የታዘቡበት ነው። በዘንድሮው ሱባዔ ደግሞ የከርሞውን አሻግረው በመመልከት የተሻለውን እየመረመሩና እየፈተኑ ለመኖር መፈጠራቸውን እንዳይዘነጉ ፍልሰታን ተጠቅመዋል። አሁንም በአታቸውን ያለቀቁ የፍልሰታን ሱባዔ በመጠቀም ላይ ጥቂት

ሊኖር ይችላሉ።

አባቶቻችን፡- “ወፈድፋደሰ ንብል . . . . . እንዘ ንሕነ ውስተ ዛቲ አሐቲ ልሕኵት ሰመዮ ሥጋ ዚአነ አብያተ ዘጽቡር እስመ ነፍሳቲነ ሕዱራት ውስቴታ”(ሃ አ ም ፹፩፡፲፩” ማለትም፡- የሰውነት መለኪያችን ከእንስሳት የምንለይበት ከፈጣሪ ጋራ የምንመስልበት በሥጋችን ያለቸው ረቂቅ የማሰብ ኃይላችን ናት። እንዳትቆሸሽ እንዳትረክስ እንዳትጎድፍ የምንጠነቀቅላት በፈራሹ ሥጋችን ያለችው መንፈሳችን ናት።” እያሉ ፍልሰታን ተጠቅመውባታል። ፈለጋቸውን በመከተል እኛም ያለንበትን ዘመንና የሚካሄደውን እንድናጤንባት ቅብብሎሹ ያስገድደናል።

ፍልሰታ ፡- እርስ በርስ በመሳመጥ ላይ ካለው ተመናዊ (ዘንዶነት) ራሳችንን አግልለን“ኦ እግዚኦ አምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአንሳእክነ እምድር ወአልአልከነ እመሬት ከመ ታንበረነ ምስለ መላእክቲከ ወመስለ መላእክተ ሕዝብከ” (ሥ ቅ ገ ፳፪፡፳፫) ማለትም፡- ከአፈር ፈጥረህ ሰው አድርገህ አቆምከን። ብንወድቅም ከወደቅንበት አንስተህ ከመላእክትና በቅድስና ከማእረገ መለእክት ከደረሱት ቅዱሳን ጋራ ታከብረናለህ።” እያልን በሩጫና በመቃተት የምንፈጽመውን በጥሞና በማስተዋልና በተረጋጋ መንፈስ የምንመረምርባት ናት።

ትኩረታችን እንጉርጉሯች የተመሰረቱት፤ የአባ ጊዮርጊስ ስሜት እና ትኩረት የተመሰረቱባቸው ሰአታት በተባለው መጽሀፍ ነው። በዚህ መጽሀፍ እየተመራን፤ “እመኒ ወደቁ እትነሳእ ነሲእየ ሰለስተ አስማተ እትመረጎዝ። ወእመኒ ሆርኩ ውስተ ጽልመት እግዚአብሔር ያበርህ ሊተ” ብወድቅም የሰላሴን ረድኤት ተመርኩዤ እነሳለሁ። ጉዞዩ በጨለማ ውስጥ ከሆነብኝም እግዚአብሔር ያበራልኛል” እያልን ሰአታትን፤ ዕለታትን፤ ወራትንና ዘመናትን በማሰላሰል፤ የሚውጠውን ብቻ ከሚያስብ ዘንዶ ልዩ የሆነውን ሰባዊነታችንን እናደንቃለን።

“ዘገብሮ ለአዳም በዘዚአሁ አርአያ ወአምሳል” እያልን በኛና በፈጠሪያችን መካከል ያለውን ረቂቅ አርአያነት እንመረምራለን። “በተነ ጊሜ ረቂቅ ዘየአቁሮ ለማይ ወያወርዶ እምኑኅ ሰማይ” ማለትም፡- በረቂቅ ተን ውህን ታሸከማለህ፤ ወደ ኑኅ ሰማይ ታወጠዋለህ። እንደገና ወደ ምድር ታወርደዋለህ” እያልን መግቦቱን ከሀሊነቱን እናደንቃለን። የተነ ጊሜ ዑደት በመሬት ያለውን ጠባየ ፍጥረት መለዋወጡን በልዩ ዜማ እናንጎራጉራለን።

በዚሁ መጽሐፍ እየተቃኘን በኛና በፈጠሪያችን መካከል ያለውን ረቂቅ አርአያነት ማሰባችንን በመንፈቀ ሌሊት እንጀምና፤ “ገባሬ መላእክት አበ ኩሉ ሠርጎ ዓለም ሣራሪሃ ለምድር ጥበብ ወአዕምሮ እምአብ ዘሀሎ እምቅድም ውስተ ዓለም ተፈነወ ዝ ህሉና ዘኢይትነሰት ወዘ ኢይተረጎም መንፈስ ዘኢያስተርኢ” ። ይህም ማለት፡- የጥበብና የአዕምሮ ባለቤት፤ የሁሉ አባት፡ ዓለምን የፈጠርክ፡ ቅድመ ዓለም የነበርክ፤ በማይመረመርና መግለጽ በማይቻል መንገድ ሰባዊነትን ለማዳን ከአብ ዘንድ የተላክ” በሚለው በነግሁ ኪዳን የየእለቱን ሱባዔ እንደመድማለን።

ይህች ዓለም ያልነበረችበት ጊዜ ነበር። አሁን አለች። ክርስቶስ የተናገረው የህልውናዋ ሱባዔ የሚቆምበት ሰአት እስኪደርስ ድረስ ወደፊት ትኖራለች። አሁን እኔ አለሁባት። እሷም አለችብኝ፤ እኔ በሷ የማልኖርበት፤ እሷ በኔ የማትኖርበት ጊዜ ደግሞ በቅርቡ ይመጣል። እስኪዚያ ድረስ ምን እያደረኩ እቆያለሁ? ትላንት በላሁ ተኛሁ ተነሳሁ። ዛሬ እየበላሁ እየተኛሁ እየተነሳሁ ነኝ። ነገ እበላለሁ እተኛለሁ እነሳለሁ። እየበላሁ እየጠጣሁ እየተኛሁ እየተነሳሁ የማልኖርባት ያችን ጊዜ እጠብቃለሁ? ታዲያ ፈጣሪ ወደዚህ ዓለም ያመጣኝ እየበላሁ እየተኛሁ እየተነሳሁ ብቻ ትንሿን ህይወቴን ላሳልፍባት ነው? ይህ ከሆነ የማስብበትንና ሀሳቤን የምገልጽበት በሀለፊ በኩነትና በመጽያት ላይ የተመሰረተውን ቋንቋየን ገና አልተገነዘብኩትም ማለት ነው። ይህም ከሰባዊ ሱባኤ ተንሸራቶ ግራ ቀኝ ማየት ወደ ማይችለው ከዘንዶ ሱባዔ መግባት ነው።

# ትልቁ ሱባኤ ምንኩስናና ገዳም ነው!

ከላይ እንዳልኩት ሰው የሆነ ሁሉ “ወባህቱ ፈቃዱ ለእግዚአብሔር አምላከ ጸጋ ንኩን ማእምራነ ቦቱ በልብ ዘሥጋ ወሰበ ነአምሮ ወነአምን ቦቱ ንከውን ደቂቀ እግዚአብሔር ወውሉደ ጥበብ ወመካነ ለምግባረ ሠናያት ወመፍቅርያነ ኂሩት ወጸላእያነ ለእከይ ወቀንያነ ለግብሩ ከመዝ”( ሃይ አ ም ፲፱፡፴፫)” እንደተባለው፤ ማለትም፡- ማንም ክርስቲያን “በአርያውና በምሳሌው የፈጠረኝ አምላክ ከኔ የሚጠብቀው በሱ ምሳሌነቴ አዋቂ አስተዋይና የጥሞና፤ የጥበብ፤ የምህረት፤ የይቅርታና የፍቅር ምንጭ፤ እንድሆን ነው። በተቃራኒው ዘንዶነትን ክፋትንና ቂምን የምዋጋ እንድሆን ነው።” ብሎ እያሰበ እያሰላሰለ ተጠንቅቆ መኖር አለበት።

ምንኩስና ግን “ይህችማ ምንላት” ብሎ ክርስቲያን እንዲያደርገው የታዘዘው ሁሉ አነሰኝ ከዚያ የራቀ፤ የረቀቀና እጅግ የላቀ ስራ መስራት አለብኝ ብሎ፤ ምሎ፤ ተገዝቶ፤ ሞቶና ተገንዞ የሚገባበት ሱባዔ ነው። በትዳር ተይዘው ሀላፊነታቸውን ለመወጣት በመባከን ላይ ካሉት ክርስቲያኖች በአጽንኦ በአት እጅግ የተሻለ ቅዱስ በመሆን ለምሳሌነት መላ ዘመኑን የሚገባው ሱባዔ ነው።

“ወዝንቱ ውእቱ ሕይወቶሙ ለደቂቀ ቤተ ክርስቲያን እንተ ሐዋርያት ወፈድፋደሰ ለእለ የሀድሩ ውስቴታ ተጋዳልያን መነኮሳት ወይደልዎሙ ይንግርዎሙ ለደቂቆሙ ይኩኑ ከመዝ። ወለእመሰ ኢይንግርዎሙ ለደቂቆሙ ይኩኑ ከመዝ፤ ኢይበሉ ንህነ ክርስቲያን ወንድህን”( ፴፬) ማለትም፡- “የሚመነኩሱት ለእውነት እንሞታለን። በዚህች ዓለም ምኞት አንሸነፍም ብለው ብቻ አይደለም። ምሳሌነታቸውን ለሚመለከቷቸው እንዲያተምሩ ነው። ይህን ባያስተምሩ በትሩፋት ተጋድሎ የሚገኘውን ን የቅድስና ዋጋ ሊያገኙ ይቅርና፤ ያልመነኮሰው ህዝብ የሚያገኘውን ጸጋና በረከት ያጡ ናቸው” ተብሏል።

በመግቢዋ ላያ ከቦታው ስንደርስ እንመለከተዋለን ያልኩትን እዚህ ላይ ላምጣውና፤ ሰለ ሱባኤ ስንነጋገር፤ በትዳር ተወጥሮ በመቃተት ላይ ካለው ህዝበ ክርስቲያን እጅግ የወረዱ መነኮሳት ቆሞሳትና ሊቃነ ጳጳሳት እንደተፈለፈሉ ተመልከተናል። ወደ ዕብራውያን በተላከው መልከት "አንድ ጊዜ ብርሃን በርቶላቸው ሰማያዊውን ስጦታ ተረድተው ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች የሆኑትን፤ መልካሙን የእግዚ ቃልና የሚመጣውን ዓለም ተረድተው ከተረዱ በኋላ የካዱትን፤ እንደገና ወደ ንስህ መመለስ አይቻልም። ምክንያቱም በክፋታቸው የእግዚ ልጅ እንደገና ሰቅለውታል"(ዕብ ፮:፮)። ተብሎ የተነገረውን በተግባር በማዋል ላይ ያሉ ጵጵስናውን ምንኩስናውንና ቅስናውን ያፈራረሱ ብዙ ናቸው።

እነሱም ዶ ክተር አረጋዊ በርኄ፤ *"የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያናን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው።"* ብለው በገለጹት የጥፋት ኮርስ እየተመለመሉ የገቡ ናቸው። በስፋት ለመረዳት ከፈለጉ "የነ ፋሌቅ ወጥመድ" በሚል ርእስ የተጻውን ጦማር ያንብቡ። ]

ዶ ክተር አረጋዊ እንደነገሩንና በተግባርም እንዳየነው፤ ከፓትርያርክነት ጀምሮ እስከ ቁምስና ድረስ እነ አቶ ስብሐት ነጋ ገብረ ኪዳን ደስታና አቶ መለሰ በዘረጉት "ባአስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር" በተዋቀረው አመራር ሰልጥነው የተሰማሩ ካድሬዎች ናቸው።

ይህም አመራር የመነኮሳቱን የቆሞሳቱንና የሊቃነ ጳጳሳቱን ባህርይ የቀየረ ነው። ጵጵስናው ምንኩስናው ቅስናው የሰውነቱን ሙቀት "በ50 degrees Fahrenheit እንደሚያበርደው ዘንዶ፤ በኮርሱ የተሰማሩት እንደ አባ ፋኑዔል ያሉ ጳጳሳት ቆሞሳት መነኮሳት የቤተ ክርስቲያናችንን መንፈሳዊ ልዕልና አውርደው ጥለውታል።

የበላውን ለማጣጣም፤ የሰበሰበውን ገንዘብና ንብረት ለመቁጥር፤ ለመዝናናት የሚያደርገውን መገለል (ድብታ) ሱባዔ ገባሁ ይላል። በመዝናናት በሽርሽር በህክምና አሮጌውን ገላውን ሽልቅቆ ካስወገደ በኋላ፤ ቀደም ብሎ የተጠቀመበትን ማስመሰያና ማታልያ መንገድ ይቀይርና ባዲስ ኃይልና ጉልበት የሚውጠውን ፍለጋ በካካባቢው አየር ንብረት እየተገፋ ያገኘውን ለመዋጥ በመቅበዝበዝ እየተንቀሳቀሰ ነው።

ለዘረፋው ይመቸው ዘንድ ያልገባቸውን ሴቶች ዕልል የሚያሰኙ ቀራፊዎችን ያሰልፋል። [ስለ ቀርፊዎች የበለጠ ለማወቅ *የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ይመልከቱ።* ቀራፊ ]። እልል በሉ እያለ ግርግርና ጫጫታ ይፈጥራል። የመቅነዝነዝ ኃይሉን ካካባቢው አየር ንብረት ጋራ እያስማማ እንደ ሚንቀሳቀሰው ዘንዶ የዘመኑ ጵጵስናም ካካባቢውና ከወቅታዊው ከወያኔ መርሆ ጋራ እያስማማ የሚውጠውን ይፈልጋል። ያሳደገውንና ያለመደውን ቢጤውንም እንደሚውጥ ዘንዶ ፤ የዘመኑ ጵጵስናና ምንኩስና እርስ በርሱ ይዋዋጣል። ህዝቡ ወዶና ተታሎ የሚሰጠው ገንዘብ አላረካው አላጠግበው ሲል፤ ያሳደገውንና ያለመደውን ህዝበ ክርስቲያን የሚሊዮን ዶላር ካሣ ከፈለኝ ብሎ ባደባባይ ይከሳል።

የኢትዮጵያ ሊቃውንት አባቶች "ዘመን ሲከፋ ሰው እርሱ በርሱ የሚባላ ዘንዶ ይሆናል"ብለው ሲናገሩ የሰማሁትን፤ የተፈጥሮ ሳይንስ ሊቃውንት እባብ ተመሳስይ መጠን ያለውን ሌላውን እባብ ሲውጠው በገሀድ አቀረቡት። ስመለከተው ያሁኑ ሁኔታችንን አብራርቶ ስላቀረበው እጅግ ዘገነነኝ።

ጵጵስና እንደ አባ ፋኑኤል አዲስ ተክል ምንኩስናና ቁምስና ደግሞ እንደ አቶ ሲሳይ ታደሰ ከሆነ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን አለቃ ገብረ ሐና እና የዲሲው መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን መስራች መላከ ገነት ውቡ ወደ ተናገሩት ማዘንበል የሚኖርባቸው ይመስለኛል።

ያለቃ ገብረ ሐናን ላስቀድም። ወይዘሮ ማዘንጊያ የሚባሉት ባለቤታቸው ለራት ሽሮ ሲሰሩ በማማሳያው እንጨት ቅምሻውን አበዙት። አለቃ ታዘቡና "ማዘንጊያ ራታችን እሱ ከሆነ እኔም መቋሚያ ይኽ ልቅረብ" አሉ። መላከ ገነት ውቡም ተመሳሳይ ነገር ተናግረዋል። በዲሲ መድኃኔዓልም መስራቾች በነ ኮረኔል አስፋው አንዳርጌ እና በአቡነ ማትያስ መካከል የጋለ ጸብ ተነሳ። አቡነ ማትያስ መላከ ገነት ውቡን ከነ ኮረኔል አስፋው ጋራ ደርበው ተገቢ ያልሆነ ቃል ተናገሯቸው።

መላከ ገነት ውቡ "ጵጵስና እንደ አባ ማትያስ ከሆነ፤ እኛም ወደ ዳውን ታውን እየሄድን ቆቡን እያሰራን፤ ልብሱን እያሰፋን ለብሰን ብቅ እንበል" አሉ። ጵጵስና እንደ አባ ፋኑዔል፤ ቁምስናና ምንኩስና ደግሞ በዚህ አመት ፍልሰታ አባ ፋኑዔል ለታደሰ እንደሰጡት ከሆነ፤ በሞራል በዝሙት በስርቆት በሀሰት የተከሰሰ ወንጀለኛ ሁሉ ቆቡን እያሰፋ ጥቁሩን ልብስ እየለበሰ ወደ ቤተ መቅደስ መግባት ሊኖርበት ነው ማለት ነው።

ይቆየን።

ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ።

http://www.medhanialemeotcks.org/